የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ለሚፈፀምባቸው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

**ጉዳዩ፡- <u>ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ /በፍራንኮቫሉታ/ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ስለሚሰጥ የጉምሩክ አገልግሎት ይመለከታል፤</u>**

መንግስት በቅርቡ ተግባራዊ ባደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ የውጭ ምንዛሪ በገበያ አማካኝነት እንዲወሰን ማድረጉን ተከትሎ ብሔራዊ ባንክ ስለአፈፃፀሙ መመሪያ ቁጥር FXD/01/2024 በማውጣት ውሳኔው ከ22/11/2016 ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህንን የመንግስት ውሳኔ በመከተል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴርም በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/641 ቀን 13/12/2016 በጻፈልን ደብዳቤ የገቢ ንግድ ስርዓቱን ይበልጥ ለማሳለጥ ይቻል ዘንድ ወደ አገር እንዳይገቡ በህግ ክልከላ ከተደረገባቸው ዕቃዎች፣ የነዳጅ አውቶሞቢሎች እና ከፀጥታና የደህንነት ዕቃዎች ውጪ ያሉ ሌሎች ገቢ ዕቃዎች ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ /በፍራንኮቫሉታ/ አገር ውስጥ እንዲገቡ በመንግስት መወሰኑን አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም የገንዘብ ሚኒስቴር በገለፀልን በዚሁ ውሳኔ መሠረት ወደ አገር እንዳይገቡ በህግ ክልከላ ከተደረገባቸው ዕቃዎች፣ የነዳጅ አውቶሞቢሎች እና ከፀጥታና የደህንነት ዕቃዎች ውጪ ያሉ ገቢ ዕቃዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 10 ንዑስ/አንቀፅ 1(ሐ) ውጪ የሚገኙ ሁሉም ሰነዶች ተሟልተው እንዲቀርቡ በማድረግ አስመጪዎች ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ /በፍራንኮቫሉታ/ ዕቃዎቻቸውን አገር ውስጥ ማስገባት የሚችሉ መሆኑ ታውቆ በውሳኔው መሠረት የተሟላ ሠነድ እንዲያቀርቡ በማድረግ በዚሁ አግባብ ለሚያስመጧቸው ዕቃዎች ህጋዊ የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ፈፅመው እንዲስተናገዱ ሆኖ በውሳኔው መሠረት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ /በፍራንኮቫሉታ/ አገልግሎት የተሰጣቸው አስመጪዎችና ዕቃዎች ዝርዝር መረጃ በተሟላ አግባብ ተይዞ በየወሩ በቋሚነት ለጉምሩክ ኮሚሽን የኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ሪፖርት እንድታቀርቡ እያሳሰብኩ፤ የገንዘብ ሚኒስቴር ያሳወቀበትን 01 ገጽ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>**ግልባጭ፤**</u>

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

<u>አዲስ አበባ</u>

- ለጉምሩክ ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ማዕከል
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኤክስፖርትና ወጪ ንግድ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

# MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No ታ/ሸ/ሎ/6/6-4/1

ቀን / Date 13/12/2016

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ፤</u>

**ጉዳዩ፦ <u>ያለ ውጭ ምንዛሬ ክፍያ (በፍራንኮ ቫሉታ) ዕቃዎችን ወደ አገር ማስገባትን ይመለከታል፤</u>**

መንግሥት በቅርቡ ተግባራዊ ባደረገው የተሟላ የኢኮኖሚ ማሻሻያ የውጭ ምንዛሬ በገበያው አማካኝነት እንዲወሰን ማድረጉ እና ይኸው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተግባራዊ መደረጉ ይታወቃል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የገቢ ንግዱን በይበልጥ እንዲያሳልጥ ወደ አገር እንዳይገቡ በሕግ ክልከላ ከተደረገባቸው ዕቃዎች፤ የነዳጅ አውቶሞቢሎች እና ከፀጥታና ከደህንነት ዕቃዎች ውጪ ሌሎች ዕቃዎች ያለ ውጭ ምንዛሬ ክፍያ (በፍራንኮ ቫሉታ) ወደ አገር እንዲገቡ በመንግሥት የተወሰነ በመሆኑ ይኸው ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

አሕመድ ሽዴ? [signature]

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
  <u>አዲስ አበባ፤</u>

በኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር 1
No 1
Ethiopian Customs Commission
Records Documentation